# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 315 ግንቦት 15 2006


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ከወያኔ ፍትህም ሆነ የህዝባችን መሰረታዊ ችግር መፍትሄ አይጠበቅም። ከእባብ እንቁላል ርግብ መጠበቅ አይቻልምና።

ግንቦት 7 የየፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ የአንዱ ብሄረሰብ ችግርየሚፈታው የሁላችንም ችግር ሲፈታ መሆኑን ያምናል። የተናጠል ትግላችን ከሚያስጠቃን በቀር ውጤት የለውም ብሎ ያምናል።

በእኛ የግንቦት 7 አስተያየት የሰሞኑ የወያኔ ጭካኔና ደባ ከቁጭት ዘሎ የዘላቂ መፍትሄ መፈለጊያ እድል አድረገን ልንጠቀምበት ይገባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአባቶቻችን በደም የተከበረዉን መሬት በፊርማ አናስከብርም- የሱዳን ድንበር አካላይ ኮሚቴ

ምንም እንኳ የሀገራችንን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት ቆርጦ የተነሳው ወያኔ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለ ነገር የለም እያለ ሲያስተባብል የቆየ ቢሆንም ባለፈው ሳምንት አንድ የድንበር አካላይ ቡድን ልኮ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያደረገው ሙከራ የተላኩት ኮሚቴዎች ከእኛ አቅም በላይ የሆነ ነገር ለመፈረም ፈቃደኛ አይደለንም በማለታቸው ለጊዜው እንደከሸፈ ተጠቆመ።

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ "ከዚህ በፊት አባቶቻችን ከሱዳን ጋር የተስማሙበትን ድንበራችንን የመከለል ስራ ነው የሚሰራው" እያለ ሕወሃት መራሹ ወያኔ ፐሮፓጋንዳ ሲነዛ መክረሙ ይታወሳል። ይሁን እንጅ በሕወሃት ሽፋን እየተሰጠው ውስጥ ለውስጥ ሲብላላና ሲንከባለል የከረመው ወገናችንን አፈናቅሎ ለም መሬታችንን ለሱዳን የማስረከቡ ሂደት ወያኔ ድንገት በፈጠረው የአባይ ግድብ ምክንያት ሱዳንን ዋና ወዳጅ አድርጎ ለመያዝ ሲባል በፍጥነት እንዲፈጸም ለማድረግ ሕወሃት እየተሯሯጠ መሆኑም ታውቋል። ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ውድ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ ጊዜያት አስፈላጊውን መረጃ ጭምር በማቅረብ የወያኔን ድንበር የማስረከብ ሩጫ እንዲገታ ለማድረግ የተለያዩ ጽሁፎችን ቢያወጡም ፋሽስት ወያኔ ግን ዓላማው ሀገር ማፍረስና ታሪክ ማጥፋት ነውና ወገን የማፈናቀሉን ስራ ገፍቶበት እንደከረመ ሲዘገብ መቆየቱም የሚታወስ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን በሰላማዊ ሰልፍና ፒቲሽኖችን በማስፈረም ጭምር ሕወሃት መራሹ ወያኔ ከሚያደርገው አፍራሽ ድርጊት እንዲቆጠብ፣ ወገኖቻችንን ማፈናቀሉን እንዲያቆም እንዲሁም ለሱዳን ለማስረከብ እያጸዳው ያለውን ለም መሬታችንን ከማስረከብ እንዲታቀብ ሲጠይቁ መቆየታቸውም ይታወሳል።

ይሁን እንጅ ይህን ሁሉ ዓለማቀፍ ተቃውሞና ውግዘት ከምንም ያልቆጠረው ፋሽስት ወያኔ በኢትዮ-ሱዳን ድንበር አካባቢ የሚኖረውን ወገናችንን

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የሕወሃት 40/60 የቤት ግንባታ ፕሮግራም ችግር እንደገጠመው ተጠቆመ

ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ማሚያ ገንዘብ ማግኛነት በሚል ልክ እንደአባይ ግድብ ድንገት ወደ ትግበራ የተሸጋገረውና በተለይ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰብ ለማለብ ታቅዶና ተስተካክሎ የቀረበው የ40 በ60 ቤት ግንባታ ፕሮግራም ከዓመት የተጠናከረ ትግበራ በኋላ የእቅዱን 12በመቶ እንኳ ለመፈጸም እንደማይችል ተጠቆመ።

የትየለሌ ወጭ በማፍሰስ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን የተሰጠው ይህ የጋራ ቤቶች ግንባታ ፕሮግራም መጀመሪያም ዓላማው ቤት መገንባት ሳይሆን ብር መሰብሰብ ነበርና 10000 የጋራ ቤቶችን ሰርቶ ያስረክባል ሲባል ከ1200 የማይበልጡ ቤቶችን ከዚህም ከዚያም ለቃቅሞ እንደሚያስረክብ መናገሩ ብዙዎቹን አስደምሟል። በተለይ ወያኔን አምነው በውጭ ሀገር እየተንከራተቱ በመከራና በችግር እየተራቡ አጠራቅመው የሚልኳትን ገንዘብ ከወሰደ በኋላ እንዲህ አይነት አሰዛኝ ዜና ማቅረቡ በውጭ የሚኖሩትን ኢትዮጵያዊያን አበሳጭቷል። በዚህ አይነት የግንባታ ዘገምተኛነት ለተመዘገበው ሁሉ ቤት ሰርቶ ለማስረከብ ሁለቴ ቢወለዱም አይደርስም የሚሉ አናዳንድ ታዛቢዎች "በቃ ሕወሃት መራሹ ወያኔ የሕዝብን ገንዘብ ቀምቷል"። "ምክንያቱም ባሁኑ ሰአት ማናቸውም ቢሆኑ በዚህ የጋራ ቤት ማሰሪያ ስም ያስቀመጡትን ገንዘብ ማውጣት ቢፈልጉ እንኳ የሚቻል አይደለም" ያላሉ። ፋሽስት ወያኔ ከአባይ ግድብ ግንባታ ጋር በተያያዘ ሙሉ የሰራተኛ ደመወዝን አስገድዶ ከመንጠቅ ጀምሮ የግዳጅ ቦንድ ሽያጭንና ያለ ፍላጎት እርዳታ እንዲለግሱ ማስገደድን ያካተተ ማፍያዊ የሌብነት ስራ በኢትዮጵያዊያን ላይ ማድረሱ ይታወሳል። ፋሽስት ወያኔ፣ ባንዳንድ ቦታዎች፣ ድጋሚ ደሞዝን የመንጠቅ ስራ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በያአካባቢው "በቃን አንከፍልም" የሚሉ ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎች በመበርከታቸው የተነሳ መቋረጡም አይዘነጋም።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔ ዘረኞች የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ አባላትን ለማሰር እንቅስቃሴ ጀመሩ

በአዲስ አበባ ካሳንቺስ አካባቢ ከሚገኘው የደህንነት ምስጢራዊ ቢሮ ውስጥ በተደረገ ዝግ ስብሰባ ላይ የተካፈለ አንድ ለድርጅታችን ቅርበት ያለው የደህንነት አባል ያደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ በስፋት የሚንቀሳቀሰውን አንጋፋ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት የሆነውን እና የፋሽስቱ ወያኔን መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ማለትም የንፁሃን ዜጎችን ግድያ፤ እስርና መፈናቀል እየተከታተለ ለአለማቀፍ ተቋማት በማጋለጥና በማውገዝ የሚታወቀውን የሰብአዊ መብቶች ጉባዬ ድርጅት በምህፃረ ቃሉ ሰመጉ አባላትን ለማሰርና ድርጅቱን ለማፍረስ እቅድ መንደፉ ታውቋል።

ፋሽስቱ ወያኔ የሰብአዊ መብቶች ጉባየ አባላትን ለማሰር በእስር ላይ ካሉ ጦማሪያን እና ጋዜጠኞች ጋር ተመሳሳይ ሊባል የሚችል የፈጠራ ክስ በማደራጀት ላይ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በአገሪቱ ሁከት የመፍጠር እቅድ ውስጥ ተንቀሳቅሷል፤ የሃገሪቱን እና የአገዛዙን ስም በአለማቀፍ መድረኮች ያጠፋል .. የሚሉ መሰረተቢስ ክሶች እንደተዘጋጁና አባላቱም ላይ ከፍተኛ የሆነ ሚስጥራዊ ክትትል እየተደረገ እንደሆነ ታውቋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሰመጉ አባል ሆነው በፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ የተባሉ እንዲሁም በተለያዩ ድህረገፆች ላይ የሚጽፉ እና ከደህነንት አካላት ጋር መረጃ የማይለዋወጡ ጋዜጠኞችም ጭምር እንዲያዙ መመሪያ መነደፉ ታውቋል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ፋሽስቱ ወያኔ የሶማሊ እና ኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎችን ለማጋጨት እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ታወቀ

በነፍሰ በላው የህወሓት አገዛዝ አቀናባሪነት በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የተጀመረው እንቅስቃሴ የሶማሊ ተወላጅ ተማሪዎች ከኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ጋር ለማጋጨት ያለመ መሆኑ የታወቀ ሲሆን የፋሽስቱ ወያኔ ካድሬዎች " የሶማሊ ተማሪዎች ከነፍሰ በላው የወያኔ አገዛዝ ጎን ቆመው በኦሮሞ ተማሪዎች ዙሪያ መረጃ እየሰጡን ነው" የሚል አሉባልታ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እየነዙ እንደሚገኙ ታውቋል። በፋሽስቱ ወያኔ ካድሬዎች እየተነዛ የሚገኘውን የጥፋት አሉባልታ ተከትሎ የሶማሊ ተማሪዎች ስጋት ላይ የወደቁ ሲሆን ተማሪዎቹ ከነፍሰ በላው የወያኔ አገዛዝ ጎን አለመቆማቸውን በመናገር የኦሮሞ ተወላጅ ወገኖቻቸው ይህንን የፋሽስቱ ወያኔ ሴጣናዊ ሴራ ጆሮ ባለመስጠት እንዲያከሽፉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ጉዳዩ በተማሪዎቹ ወላጆች ጭምር መደናገጥ መፍጠሩ ታውቋል። ነፍሰ በላው የህወሃት አገዛዝ የተለያዩ ብሄረሰብ ተወላጆችን ለማጋጨት እንቅስቃሴ መጀመሩን በተመለከተ ተከታታይ ዘገባዎችን ማቅረባችን ይታወሳል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ዲፕሎማቱ እራሳቸዉን አጠፉ ቢባልም የአሟሟታቸዉ ምክንያት አሁንም በዉል አልታወቀም

ባለፈዉ ሳምንት መግቢያ ላይ ከመደበኛ የስራ ሰአት ውጭ ከጧቱ 1 ሰአት ተኩል አካባቢ ወደ ቢሮአቸው ገብተዉ ራሳቸውን ከፎቅ ወርውረው ገደሉ የተባሉት የ62 አመቱ ዲፕሎማት የአቶ ፍሰሃ ተስፉ አሟሟት ምክንያቱ ባለመታወቁና መንግስትም የድፕሎማቱን አሟሟት አስመልክቶ የሰጠዉ መረጃ ባመለኖሩ ብዙዎችን ግራ አጋብቷል። ከድፕሎማቱ ሞት ሁለት ናት በኋላ ታትሞ የወጣዉ ክሮናካ ዲ ሮማ የተባለው የጣሊያን ጋዜጣ ዲፕሎማቱ ከመሞታቸው ከሁለት ቀናት በፊት ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ተነግሮዋቸው እንደነበር አንዳንድ ጓደኞቻቸውን ጠቅሶ የዘገበ ቢሆንም ሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው ግን ዲፕሎማቱ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ስለመታዘዙ እንደማያውቁ ተናግረዋል።

ጋዜጣው እንደዘገበው ዲፕሎማቱ ራሱን ያጥፋ ወይም ሌላ ሰው ይግደለው እንደማይታወቅ ገልጾ፣ ራሱን ካጠፋ ግን አንድ መልእክት ለማስተላለፍ አስቦ ያደረገው ሊሆን እንደሚችል የፖሊስ ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል። በዲፕሎማቱ ቢሮ ውስጥ ምንም አይነት ማስታወሻ አለመገኘቱን፣ የተዘበራረቀ ነገር አለመኖሩንም የገለጸው ጋዜጣው፣ የረጅም ጊዜ ዝግጅት የተደረገበት ነበር ብሎ ለመናገር እንደማይቻልም አትቷል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በራችንን ከፍተን የወያኔን ሌብነት ማቆም አንችልም! ግንቦት 7

የወያኔ ጉጅሌና ሎሌዎቹ ስልጣናቸውን በህዝብ ፈቃድ ላይ እንዳልቆመ አሳምረው ያውቃሉ። ነጻ የህዝብ ምርጫ ቢኖር ምን እንደሚሆኑ የዛሬ ዘጠኝ አመት በአይናቸው አይተዋል፣ በጆሮቸው ሰምተዋል። ከዚያ ተመክሮ ተነስተው ዳግም የህዝብ ፈቃድ ላለመጠየቅ ምለዋል። ቅዱሱን የዴሞክራሲና የፍቅር መንገድ ሳይሆን ሳይጣናዊውን የከፋፍሎና አናክሶ የመግዛትን መንገድ ዋና ምርጫቸው አደርገው ከወሰዱ ሰንብተዋል። የፍትህና የዴሞክራሲ ሂደት በኢትዮጵያ እነሱ እስካሉ ድረስ እንዳይነሳ አድረገው ቀብረውታል። በራሳቸውና ጥቅማቸው ላይ ኮሽታ በመጣባቸው ቁጥር ችግሩ በምስኪኑና የነሱ ሰለባ በሆነው ህዝብ ውስጥ መካከል እንደተፈጠረ ግጭት ለማስመሰል እና ለማድረግ የማያደርጉት ነገር የለም።

ወያኔ ሰሞኑን በመላው የኦሮሞ ተወላጆች የመጣበትን ተቃውሞ የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች ጠብ ለማድረግ ያላደረገው ነገር የለም። መሰረታዊ የሆነውን የኦሮሞ ተማሪዎች ጥያቄ የባህርዳር እና በሌሎች የሀገሪቱ የሚገኙ ተማሪዎች ደግፈው ሂወታቸውን ያጡለትን የጋራ የወገንን ጥያቄ ለመቀልበስና፣ የኦሮሞና የአማራ ህዝብ ጠብ ለማድረግ ያላደረገው ጥረት የለም።

መሰረታዊ የሆነውን የኦሮሞ ተማሪዎች ጥያቄ በጥይት ብቻ ሊመልሰው እንደማይችል የተረዳው ወያኔ፤ በግርግሩ ውስጥ አማሮችና ኦሮሞዎች ደም እንዲቃቡና እንዲጋጩ አድርጎ ገላጋይ ለመምሰል የሚያደርገው ሙከራ ባይሳካለትም ይህን ተንኮል በህዝቡ ውስጥ የመትከል አባዜ ስራውን በስፋት ተያይዞታል። ሰሞኑን በመላው ኦሮምያ ካድሬ በማሰማራትና ገላጋይ በመምሰል ዋናውን የወያኔ መሬት ዝርፊያ ይቁም የሚለውን ጥያቄ በማለባበስና በማፈን ዘዴ ላይ ይገኛል።

ወያኔ ይህን ስልት የመረጠው ወያኔን የምንቃወም የነጻነትና የዴሞክራሲ አንድነት ሃይሎች የትብብር ደረጃ ያለበትን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ነው። በርግጥ ይህን ሳይጣናዊ በር የከፈትንለት እኛው የነፃነትና የዴሞክራሲ ሃይሎች ነን። በመካከላችን የተቀናጀና የተባበረ እንቅስቃሴ ማድረግ አለመቻላችን በብዙ መልኩም ህዝባችን የሚያስተባብር የጋራ አመራር በመጥፋቱ ነው።

የወቅቱም ሆነ የዘላቂው ችግር መፍቻ ይህ የዴሞክራሲና የነጻነት ሃይሎች የተግባር ህብረትና ቅንጅት መሆኑን ለመማሪያ ከሰሞኑ ተሞክሯችን የበለጠ መማሪያ ያለ አይመስለንም። የወያኔ ጉልበት የተቃዋሚዎች ክፍፍል ብቻ ነው። እኛ ተጠቂዎቹ የችግሩን ማስወገጃና የዘላቂ የሀገራችንን ህይዎት የሚመራ የጋራ ራእይ አለማበጀታችን ነው። ሌባው ህዝባችንን የሚከፋፍልብን በራችንን በርግደን ስለከፈትን እና ለመከፋፈል ስለተመቸናቸው ነው። ይህን በር ከፍተን እስካቆየነው ድረስ የህዝባችን ደም በግፍ መፍሰሱ፣ ህዝባችን መዘረፉና በውርደት መኖሩ ይቀጥላል።

ከወያኔ ፍትህም ሆነ የህዝባችን መሰረታዊ ችግር መፍትሄ አይጠበቅም። ከእባብ እንቁላል ርግብ መጠበቅ አይቻልምና።

ግንቦት 7 የየፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ የአንዱ ብሄረሰብ ችግርየሚፈታው የሁላችንም ችግር ሲፈታ መሆኑን ያምናል። የተናጠል ትግላችን ከሚያስጠቃን በቀር ውጤት የለውም ብሎ ያምናል።

በእኛ የግንቦት 7 አስተያየት የሰሞኑ የወያኔ ጭካኔና ደባ ከቁጭት ዘሎ የዘላቂ መፍትሄ መፈለጊያ እድል አድረገን ልንጠቀምበት ይገባል። ይህንና ተመሳሳይ ጥቃቶችን ተባብረን መመከት ባቃተን ቁጥር የህዝባችን መከራ እያራዘምን ነው። በዚህ ወቅት ህዝባችን ከአገራችን አጽናፍ እስከ አጽናፍ አንድ ድምጽ መሰማት መቻል ይኖርበታል። የሁላችንም አይን ያን ጊዜ ወያኔና ጉጅሌዎች ላይ ብቻ ይሆናል። ወያኔ የሚደግስልን የጎን ለጎን ግጭት ድግስ የሚከሽፈው ይህን ጊዜ ብቻ ነው።

በሚደርሱን መረጃዎች መሰረት ወያኔ በተለይ በኦሮሞ ህዝብና በሌላው ብሄረሰቦች መካከል ስር የሰደደ ጠብ ለመፍጠር በመራወጥ ላይ ይገኛል። ለዚህ ተግባር የሚሆን የሰው፣ የገንዘብና የሚዲያ ሃይል አደራጅቷል። የተደገሰው የብሄር ለብሄር ግጭት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ብሄረሰብ ውስጥ ክፍፍል በመፍጠር ህዝብ የማባላት ድግስ ነው። ወያኔ ለውጪ አሳዳሪዎች የህዝቡን ደም የማፈሰው የእርስ በእርስ ግጭት ለማስወገድ ነው የሚል መልስ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ራሱ የሚያደርሰውን ጥፋት ሁሉ በተቃዋሚዎቹ እና በራሱ ህዝብ ውስጥ ባሉ ሰለባዎቹ ላይ ለማመካኘትና በዚሁ እብሪቱ ለመቀጠል መወሰኑን አረጋግጠናል።

ግንቦት 7 ዘወትር እንደሚለው ሁሉ ህዝቡ የወያኔ የተንኮል መሳሪያ እንዳይሆን የልዩነት በሩን እንዲዘጋ የቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ለሁሉም የነጻነትና ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የእንተባበር ጩኸቱንም ደግሞ ያሰማል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## በአባቶቻችን በደም የተከበረዉን መሬት በፊርማ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሃይል በማፈናቀልና በማሰደድ አካባቢውን አሳልፎ ለሱዳን ለመስጠት ከጫፍ መድረሱ ከታዋቂ ምንጮች ተረጋግጧል። ይህን ለማድረግም ባለፈው ሳምንት ታዋቂ  የሀገር ሽማግሌዎች የሚላቸውን የድንበር አካላይ ኮሚቴ በሚል ሰብስቦ ወደ ሱዳን ድንበር በመውሰድ የድንበር ማስረከቡን ሂደት በፊርማቸው እንዲያጸድቁ ለማድረግ ቢሞክርም ኮሚቴዎቹ "እኛ ድንበርን አሳልፎ ለመስጠት የሚያበቃ ስልጣን የለንም" በማለት ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሕወሃት አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባም ተያይዞ ተጠቅሷል።

ይህን ከጎንደር እስከ ጋምቤላ የሚደርሰውንና እጅግ ለምና ሰፊ መሬታችንን ለሱዳን ለማስረከብ ሲታሰብ ባሁኑ ሰአት ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር የሚባል ስልጣን የሌለው ስም የተሸከመው ደመቀ መኮንን የአማራን ክልልና ወያኔን በመወከል ከሱዳን ጋር መፈራረሙ ይታወሳል። ቦታው ግን አጼ ቴወድሮስንና አጼ የሃንስን ጨምሮ ብዙ የአካባቢው አስተዳዳሪዎች የሀገራቸውን ድንበር ለማስከበር ሲሉ ከሱዳንና ሱዳንን ተከልለው ከመጡ ዓለማቀፍ ወራሪዎች ጋር ተፋልሞ አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍስሶ ድባቅ መቶ የመለሰበት ቦታ ከመሆኑ አንጻር በታሪካዊነት ተመዝግቦና ተጠብቆ ለጎብኝዎች በሚመች መልኩ ተዘጋጅቶ እየተጎበኘ ያለፈውን ታሪክ መናገር ነበረበት የሚሉ ወገኖች ጥቂቶች አይደሉም።

ታሪክና ጀግንነት የሚያንገሸግሸው ፋሽስት ወያኔ ግን ሀገራችንና ቀደምት አባቶቻችን የሚታወቁበትን የሚያኮራ የጀግንነት ታሪክና በደምና ባጥንት የቆመ የአትንኩኝ ባይነት ኢትዮጵያዊነትን በማዋረድና በማንቋሸሽ የሚታወቅ ሲሆን፤ አባቶቻችን በሃይል ያስከበሩትን ድንበራችንን  ውሰዱልኝ እያለ በልማና ለማስረከብ ስንደረደር መታየቱ እጅግ በጣም አሳፋሪ ነው። ይህን የሕወሃት ስራ ይህ ትውልድም ሆነ መጪው ተከታታይ ትውልድ ፍጹም ይቅር የማይለው ከመሆኑም ባሻገር የጊዜ ጉዳይ እንጅ በግፍ የሚሰጥ የሀገራችን ድንበር ሁሉ በጊዜው መመለሱ አይቀሬ ነው የሚሉ ግን ብዙዎች ናቸው።

---

## የወያኔ ዘረኞች የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ አባላትን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተያያዘ ዜና ፋሽስቱ ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የውጪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የስራ አመራር አባላት ላይ ከፍተኛ ስለላ እያካሄደ እንደሚገኝ የታወቀ ሲሆን በተለይም የከፍተኛ ስራ አመራሮች የስልክ ልውውጥ እየተጠለፈ እንደሚደመጥ ታውቋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የልማት እና የበጎ አድራጎት ስራ ላይ የተሰምሩ የውጪ ድርጅቶች በመጪው የ 2007 አ.ም አገራቀፍ ምርጫ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ተከትሎ የተወያየው የወያኔው የደህንነት ቡድን በተለይ በየክልሉ በሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የስራ አመራር አባላት ላይ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ በማለት ውሳኔ በማሳለፍ፤ ለክትትሉ ስራ በጀት በመመደብና የአመራሮቹ የስልክ ልውውጦች እንዲቀረፁ ትዕዛዝ በማሳለፍ መጠናቀቁን ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል።

# የመጨረሻዉ ካርድ

አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት ያለፈችበትን የግፍና የመከራ ዉጣ ዉረድ ወደ ኋላ መለስ ብሎ መመለከት መፈጠርን የሚያስጠላና ልብን የሚያደርቅ እራሱን የቻለ ሌላ በጭንቅና በመከራ የተሞላ ዉጣ ዉረድ ነዉና አለመሞከሩ ይመረጣል። ሆኖም አገራችንን ከዚህ ሳትወድ በግድ እጇን ታስራ ከገባችበት የጥፋት ቁልቁለትና የመከራ አዘቅት ዉስጥ ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ ጎትቶ ለማዉጣት የግድ እዘህ ድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ እንዴት ገባች ብሎ እራስን መጠየቅ ያስፈልጋልና ወደድንም ጠላን የሃያ ሦስቱን አመት ጉዟችንን ወደ ኋላ ዞር ብለን በጥሞና ማጤኑ አማራጭ የሌለዉ መንገድ ነዉ። የወያኔ ዘረኞች ፋሺስቱን ደርግ ጣልን ይበሉ፤ በ99.6 በመቶ ድምጽ ተመርጥን ይበሉ ወይም እድገት አመጣን ይበሉ የእነሱ ፍላጎት ምን ግዜም ቢሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጦ መግዛት ነዉ እንጂ ህዝብን በጨዋነት ማስተዳደር አይደለም። አንድን ህዝብ ረግጦ ለመግዛት የሚያስፈልገዉ ደግሞ ጠመንጃና ባዶ ጭንቅላት ብቻ ነዉ፤ ጠመንጃና ባዶ ጭንቅላት በገፍ የሚገኝበት ድርጅት ነዉና ወያኔ ደግሞ በዚህ በፍጹም አይታማም። የወያኔ ዘረኞች ፍላጎት የኢትዮጵያን ህዝብ ከጣሊያን ፋሺስቶች ባልተለየ መንገድ እየረገጡ መግዛት ቢሆንም አንድን ህዝብ ዝንተ አለም ረግጦ መግዛት እንደማይቻል በሚገባ ያዉቃሉ፤ ለዚህ ነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ኃይሉን እነሱ ላይ ለማሳረፍ በቆረጠ ቁጥር ህዝብን ከህዝብ የሚለያይና የሚያራርቅ ካርዳቸዉን እየመዘዙ ጻረ ህዝብና ጻረ አገር ጨዋታቸዉን የሚጫወቱት። በእርግጥም ወያኔዎች በስልጣን በቆዩባቸዉ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት የተለያዩ ካርዶችን መዝዘዋል - ፌዴራሊዝም እያሉ በፌዝራሊዝም ቀልደዉብናል፤ እድገትና ልማት እያሉ ጠብ ያለዉን ሁሉ እነሱ እራሳቸዉ እየዋጡ ሌሎቻችንን የበይ ተመልካቾች አድርገዉናል፤ በጎሳ ከፋፍለዉናል፤ በዘር አጥር አጥረዉናል። ዛሬ ደግሞ ለእነዚህ ተራ በተራ ለመዘዟቸዉ የከፉት ካርዶች አልታለልም ያለዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ካዝናቸዉ ዉስጥ የቀረቻዉን የመጨረሻ ካርድ መዝዘዉ በጎሳና በዘር ከመለያየት አልፈዉ በዘር ለማጋጨትና ደም ለማፋሰስ ጉድ ጉድ እያሉ ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ማንም ኃይል በምርጫ ሥልጣን ያዝኩ ብሎ አፉን ሞልቶ ለመናገር ኦሮሚያና አማራ ክልል ዉስጥ ምርጫዉን ጉልህ በሆነ ብልጫ ማሸነፍ አለበት፤ ወይም አማራና ኦሮሚያ ዉስጥ ተሸንፎ ፓርላማ ዉስጥ አብዛኛዉን ወንበር ተቆጣጥሮ መንግስት መመስረት አይቻልም። ወያኔ ዛሬ ያንን የእንቅልፋሞች ፓርላማዉ ተቆጣጥሮ መንግስት ነኝ ብሎ የሚፏልለዉ ሁለቱን የአገራችንን ግዙፍ ብሄረሰቦች ለያይቶና አንዱ ሌላዉን በጥርጣሬ አይን እንዲመለከት አድርጎ ነዉ እንጂ ወያኔ በየቀኑ የሚያስራቸዉ፤ የሚደበድባቸዉ፤የሚያሳድዳቸዉና የሚገድላቸዉ የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች በፍላጎታቸዉ መርጠዉታማ አይደለም። ወያኔ ዛሬ ከሚታይበት የፖለቲካ ኪሳራና ህዝባዊ መተፋት አንጻር እንደቀድሞዉ ኦሮሞንና አማራን በመከፋፈልና በመለያየት ብቻ ስልጣን ላይ መቆየት እንደማይችል ስለተረዳ እነዚህ ሁለት የአገራችን ግዙፍ ብሄረሰቦች እርስ በርሳቸዉ ተጋጭተዉ እንዲተላለቁ የሚቻለዉን ሁሉ እያደረገ ነዉ። ወይም ቀለል ባለ አማርኛ ወያኔ ከጫካ ይዞት የመጣዉን የመጨረሻ ካርድ መዝዞ አገራችንን በቀላሉ ወደ ማትወጣዉ የዘርና የጎሳ ግጭት ዉስጥ ለመክተት ቁጭ ብድግ እያለ ነዉ።

ወያኔ የመሬት ባለቤትነትን ጉዳይ ህገ መንግስቱ ዉስጥ ሸንቁሮ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት የግል ንብረት የሚሆነዉ በእኔ መቃብር ላይ ነዉ ያለዉ አለምክንያት አይደለም። ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት የህዝብና የመንግስት ነዉ ይበል እንጂ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትክክለኛዉ የመሬት ባለቤት ህዝብም መንግስትም ሳይሆን ህወሀት ወይም ወያኔ ነዉ። ይህንን ወያኔ የሚባል የዘረኞች ስብስብ ባስቸኳይ ጠራርገን በገዛ አፉ እንደተናገረዉ በወያኔ መቃብር ላይ የአገራችንን የተዛባና ጎታች የመሬት ይዞታ በፍጥነት ካልቀየርን ሁላችንም የወያኔ ገባር መሆናችን የማይቀር ነዉ:። ዛሬ ወደድንም ጠላን አገራችን ዉስጥ ልክ እንደፊዉዳሉ ዘመን መሬት እንደ ስጦታ ለዘመድና ለቤተዘመድ የሚሰጥ ደሃዉንና ሀብታሙን የሚለይ የመጨቆኛ መሳሪያ ነዉ። መሬት መብት መርገጫ ነዉ፤ መሬት አፍ ማስዘግያ ነዉ፤ መሬት ማማለያ መሳሪያ ነዉ፤ መሬት የማይወዱትናን የኛ አይደለም የሚሉትን ማግለያና መድረሻ ማሳጫ ነዉ። ባጠቃላይ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት የወያኔ ቂም በቀል መወጫ አይነተኛ መሳሪያ ነዉ። ወያኔ እኔን አይደግፈኝም ከሚለዉ ከማንም ሰዉ መሬት ቀምቶ ላሰኘዉ ሰዉ መስጠት ይችላል። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ ብዙ መጓዝ አያስፈልግም፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሉ አዳዲሶቹን የከተማ ቦታና ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ መመልከቱ ይበቃል።

በቅርቡ አምቦ ዉስጥ በግፍ የተጨፈጨፉት የኦሮሞ ተማሪዎች እንደዚህ አይነቱን አግላይ የሆነ የወያኔ የመሬት ፖሊሲ የተቃወሙ ተማሪዎች ናቸዉ። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በልማት ስም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚኖሩ የኦሮሞ ገበሬዎችን እያፈናቀለ መሬቱን ለራሱ ወገኖች መስጠቱን በመቃወም አምቦ፤ ጅማ፤ ወለጋ፤ አዳማና ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የሚማሩ የኦሮሞ ተማሪዎች ወያኔንና ደጋፊዎቹን ክፉኛ ያስደነገጠ ከፍተኛ የተቃዉሞ ሰልፍ ያደረጉትና ምትክ የሌለዉን ህይወታቸዉን የገበሩት ይህ እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ የወያኔ የመሬት ፖሊሲ ስለገባቸዉ ነዉ። በዚህ በተለያዩ ቦታዎች በተካሄደዉ የተቃዉሞ ስልፍ ላይ የኦሮሞ ተማሪዎች ያነገቡት አንድ ጥየቄ ብቻ ነበር፤ እሱም ህዝብን ያላካተተ ልማት የለምና ወላጆቻችንን እያፈናቀላችሁ መሬታችንን መከፋፈል አቁሙ የሚል ጥያቄ ነበር። ለዚህ የኦሮሞ ተማሪዎች በሰላማዊ መንገድ ላቀረቡት ጥያቄ ወያኔ የሰጠዉ መልስ እንደተለመደዉ በአግአዚ ነብሰ ገዳዮች ወጣቶችን በየአደባባዩ በጥይት መጨፍጨፍ ነበር - አዎ! የወያኔ ስራ ጥያቄ ሲጠይቁት መግደል፤ ምርጫ ሲሸነፍ መግደል፤ ለምን ጻፍክ ብሎ መግደል፤ ለምን ተናገርክ ብሎ መግደል ነዉ።

ወያኔ በሃያ ሦስት አመታት የስልጣን ዘመኑ እንደ ዘንድሮ ተገፍቶ ተገፍቶ ዳር የደረሰበትና እንደ ዘንድሮ መዉጪያና መግቢያዉ ጠፍቶበት አያዉቅም። እኛ ብናምንም ባናምንም ወይም ብናዉቅም ባናዉቅም ወያኔ የተከበበ አዉሬ ሆኗል፤ ግን ከዚህ በፊት እንዳደረገዉ ሁሉ የከበቡት ኃይሎች ፊት ለፊት የሚተያዩና አብረዉ የሚሰሩ ኃይሎች ባለመሆናቸዉ ወያኔ ከበባዉን ጥሶ ለመዉጣት እየሞከረ ነዉ። ከላይ ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርነዉ ወያኔ እንደ ዘንድሮ ተዋክቦና እንደዘንድሮ የመጨረሻዉ ሽትቶት አያዉቅም። ሆኖም እንድ መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ወያኔ ከገጠመዉ ህዝባዊ ቁጣ ለማምለጥና ስልጣን እንደጨበጠ ለመቀጠል እንደዛሬ የዘር መለያየትና ማጋጨት ሴራዉን ተግባራዊ ያደረገበት ግዜም የለም። እዉነቱን ለመናገር በአንድ በኩል ምንም ጥርጥር በሌለዉ መልኩ ወያኔ ተከብቦ ህልዉናዉ አደጋ ላይ ወድቋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ከዚህ ተገፍቶ ከገባበት አደጋ ለመዳን አገራችን ዉስጥ ዘርና ጎሳ ለይቶ ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያባላ የእርስ በርስ ጦርነት ለመቀስቀስ ዝግጅቱን ጨርሷል።

የኦሮሞ ተማሪዎች ባካሄዱት የተቃዉሞ ሠልፍ ዉስጥ አልፎ አልፎ የተሰማዉ “የሚኒልክ ሃዉልት ይፍረስ” የሚለዉ ጨኸትና ጊምቢና በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ወረዳዎች አማራ ይዉጣልን የሚለዉ ጥያቄ የህዝብ ጥያቄ ሳይሆን ወያኔ ሆን ብሎ ከትኩቶ ባሳደጋቸዉ ካድሬዎቹ አማካይነት ህዝብ ዉስጥ ይዞት የገባዉ የእርስ በርስ እልቂት መቀስቀሻ ጥያቄ ነዉ። ሁለቱ ዝሆኖች ሲጣሉ የሚሰቃየዉ ሳሩ ነዉ እንደሚባለዉ ወያኔ የአማራንና የኦሮሞን ብሄረሰቦች በማጋጨት እነዚህ ሁለት የአገራችን ብሄረሰቦች እርስ በርስ ሲፋጩና የኢትዮጵያ ህዝብ ሲሰቃይ እሱ የስልጣን ዘመኑን ማራዘምና የዘረፋ ተልዕኮዉን እንደገና ማደስ ይፈልጋል። ይህ “እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይብቀል” አይነቱ የወያኔ ሴራ ለወደፊት ሊከናወን በዕቅድ የተያዘ ጥንስስ ሳይሆን ከአመታት በፊት ጫካ ዉስጥ ታቅዶ ዛሬ ተግባራዊ በመሆን ላይ ያለ የወያኔ ተንኮል ነዉ።

ወያኔ የኦሮሞና የአማራ ብሄረሰቦች እጅ ለእጅ ተያይዘዉ ከተነሱበት የስልጣን ዘመኑ በቀኖች እንደሚቆጠር በሚገባ ያዉቃል፤ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ አብዛኛዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ያቀፉት ሁለት ግዙፍ ብሄረሰቦች በመካላቸዉ ስምምነት ከሌለና አንዱ ሌላዉ ላይ በቂም በቀል ከተነሳ ማንም በቀላሉ ከስልጣን እንደማያባርረዉ ጠንቅቆ ያዉቃል፤ ለዚህም ነዉ ባገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ እንዚህ ሁለት ብሄረሰቦች እንዲጋጩ ክብሪት የሚጭረዉ። አምቦ፤ ጊምቢ፤ አኖሌና ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተደጋጋሚ የተጫረዉ የዘር ግጭት መቀስቀሻ እሳት ወያኔ አማራዉንና አሮሞዉን ለማጋጨት ሆን ብሎ የለኮሰዉ እሳት ነዉ። ዛሬ የኦሮሞን ተወላጆች ስልጣን መድረክ አካባቢ እንዳይቀርቡ አድርጎ የኦሮሚያን መሬትና የመሬት ላይና ዉስጥ ኃብት በገፍ የሚዘርፈዉና የአገሪቱን እስር ቤቶች በኦሮሞ ተወላጆች የሞላዉ ወያኔ ነዉ እንጂ ግዑዙና የማይናገረዉ የምኒልክ ኃዉልት አይደለም። አህዴድ የሚባል ተለጣፊ ባቡር ሰርቶ የኦሮሞን ህዝብ የሚገድለዉና በገዛ መሬቱ ላይ ባይተዋር ያደረገዉ ወያኔ ነዉ እንጂ ከመቶ አመት በፊት ሞተዉ የተበሩት ዳግማዊ ምኒልክ አይደሉም። ስለዚህ የኦሮሞ ህዝብ ከአማራዉና ከሌሎቹ ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር ሆኖ ማፍረስ ያለበት የምኒልክን ኃዉልት ሳይሆን ወያኔንና ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐት ነዉ።

ባለፈዉ ወር አምቦ ላይ ያየነዉ የአግአዚ ጭፍጨፋ ወያኔ ከደገሰልን ጥፋት ጋት ሲነፃፀር እጅግ በጣም ትንሽ ነዉ፤ ወያኔ እያንዳንዳችንን በተናጠል በመታና በገደለ ቁጥር ቁጣችንን የምንገልጸዉና የምንከላከለዉ በተናጠል ከሆነ ወያኔ እያንዳንዳችንን በተናጠል እየገደለም ሆነ እያሰረ ጭጭ የማስደረግ ኃይል አለዉ። ይብዛም ይነስ የወያኔን ጥቃት ተቋቁመን ወያኔን ማስወገድ የምንችለዉ በጋራ አንድ ሆነን ስንቆም ብቻ ነዉ። እያንዳንዳችን ሺ ጠመንጃ ይዘን ወያኔን በተናጠል ብንገጥመዉ አናሸንፈዉም፤ ሁላችንም ተባብረን እንደ አንድ ሰዉ መቆም ከቻልን ግን ወያኔን ለማሸነፍ ጠመንጃም አያስፈልገንም። ስለዚህ ዛሬ ለኛ ለኢትዮጵያዉያን የትብብር ጥያቄ የትግል አማራጭ ሳይሆን በፍጹም ልናልፈዉ የማይገባን የህልዉና ጥያቄ ነዉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን - ኑ አብረን እንታገል እያልን የትግል ጥሪ ስናስተላልፍ ወያኔ ደግሞ አገር እያፈረሰና ህዝብ እየገደለ ከሃያ አመት በላይ ተጉዞን ዛሬ ላይ ደርሰናል። የእኛ ጨኸት ከሃያ አመት በኋላ ዛሬም እንተባበር የሚል ነዉ፤ ሃያ አመት ሙሉ አገር ሲንድና ህዝብ ሲገድል የከረመዉ ወያኔ ግን ዛሬ የተቃወመዉን ሁሉ ቢቻል ለመግደል አለዚያም ለማሰር እየተንቀሳቀሰ ነዉ። እንደ አገርና እንደ ህዝብ በአንድነታችን ፀንተን ለመቀጠል ካሁን በኋላ ያለን ብቸኛ አማራጭ ጥቂቶች ታስረን፤ ጥቂቶች ተሰድደን ጥቂቶች ደግሞ ሞተን ወያኔን ማስወገድ ወይም በተናተል ሁላችንም ተራ በተራ መሞት ነዉ።

አባቶቻችን ያስተማሩንና እኛም በነጋ በጠባ እንደ ዳዊት የምንደግመዉ ይህንኑ ለእናት አገሬ እሞታለሁ የሚለዉን የአባቶቻችንን ትምህርት ነዉ።

ወገን ለኢትዮጵያ መሞት ካለብን ቀኑ ዛሬ ነዉ . . . . ኑና ለእዉነት ሞተን በህይወት እንኑር!

## አዲስ አበባ አሁንም የኗሪዎቿን ቤት ማፍረሱን በስፋት ተያይዛዋለች

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ዉስጥ ከአመታት በፊት የጀመረዉን የቤት ማፍረስ ዘመቻ አሁንም አጠናክሮ የቀጠለበት መሆኑን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ የሚልኩልን ዜና ያስረዳል። እብሪተኛዉና ለዜጎች ምንም ደንታ የሌለዉ ወያኔ ቤቶቹን የሚያፈርሰዉ ካለ ምንም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በድንገት ሲሆን ቤቶቻቸው የፈረሱባቸው ግለሰቦች ንብረታቸዉ አንደሚዘረፍና እነሱም መግቢያና መዉደቂያ ቦታ አጥተዉ እንደሚንከራተቱ ለማቀቅ ተችሏል። በቅርቡ ከአዲስ አበባ ከታመኑ ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሰረት አንድ ቤታቸዉ የፈረሰባቸዉ የ4 ልጆች በጅብ ተበልተው ቀሪዉ አካላቸዉ በፖሊስ ተለቅሞ መወሰዱን ተናግረዋል። ፖሊሶች መረጃው እንዳይወጣ አካባቢውን ተቆጣጥረው ሰዎች እንዳይንቀሳቀሱ ሲያደርጉ የዋሉ ሲሆን፣ ቀሪው አስከሬን ከተነሳ በሁዋላ ደግሞ በማይክራፎን እየዞሩ በላስቲክ ድንኳን የተጠጉትን ሰዎች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ እያዘዙዋቸው ነው። ብዙዎቹ ልጆቻቸውን የት እንደሚያስጠጉዋቸው ጨንቋቸው ለኢሳት በመደውል የድረሱልን ጥሪ አቅርበዋል።

ቤታቸው የፈረሰባቸው ሰዎች ለኢሳት በጻፉት የጋራ ደብዳቤ ደግሞ ፣ እንደ አዲስ ሰሞኑን የሚፈርሱ ቤቶች በዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ተስፋ በተደረገ ፈንድ ለሚገነባው የኦሎምፒክ መንደር ፕሮጀክት ቦታ ለማዘጋጀት ሲባል በመሆኑ ኦሎምፒክ ኮሚቴው የህዝቡን ስቃይ አይቶ፣ ድጋፉን እንዲያዘገይ ጠይቀዋል።ነዋሪዎቹ በደብዳቤያቸው "የኢትዮጵያ መንግስትና የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ከዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ 2 ሚሊዩን የኢትዮጵያ ብር እንደሚሰጣቸው" ገልጸዋል።"በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሦስት ቀናት ውስጥ መኖሪያቸውን ነቅለው ከአካባቢው እንዲወጡ ጥብቅ ትዕዛዝ የተላለፈው ከዚህ ፕሮጅክት ጋር በተያያዘ መሆኑን ነዋሪዎች በደብዳቤያቸው ጠቁመዋል።

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት "የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ከዚህ በፊት ቤታቸውን ነቅለው አካባቢውን እንዲለቁ በተደጋጋሚ እንደ ተገለጸላቸው የሚጠቁም ቢሆንም፣ ከዚህ በፊት ቤት ግን አንድም ቀን ነዋሪዎቹ ነቅለው እንዲነሡ እንዳልተነገራቸውና ደብዳቤም ተጽፎላቸው እንደማያውቅ" ጠቅሰዋል:: በሦስት ቀናት ውስጥ ቤቶች እንዲፈርሱ የታዘዘበት ምክንያት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት ሁሌም እንደ ሚያደርጉት የኗሪዎችን ቤት ነቅለው በመወሰድ እንጨቶችን፣ ቆርቆሮዎችን፣ በሮችንና መስኮቶችን በወረዳ አሰተዳደር ቅጥር ግቢ እያጫረቱ በመሸጥ ቤት አፍራሾቹና አመራሩ እንዲካፈሉት ለማድረግ መሆኑን ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

"የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከክፈለከተማው አስተዳደር የመጣ ትእዛዝ ነው ምንም ማድረግ አልችልም የሚል መልስ ለአቤቱታ አቅራቢዎች ሲሰጡ፣ የክፍለ ከተማው አስተዳዳሪ አቶ ደስታ ደግሞ አቤቱታ አቅራቢዎች ከቢሯቸው እንዲባረሩ ማስደረጋቸውን ነዋሪዎች በጽፉቸው አስፍረዋል። ኗሪዎች በንብረታቸው ላይ ሊካሄድ የታቀደውን ዝርፍያ በመፍራት የቤቶቻቸውን ጣራና በር አንስተው ዘመድ ያለው ከዘመድ የሌላቸው ደግሞ ላስትክ ዘርግተው በተጠለሉበት ቅዳሜና እሁድ ባለማቋረጥ የዘነበውን ዝናብ በላያቸው ማሳለፋቸውን፣ አራስ እናቶች እና አዲስ የተወለዱ ሕጻናት፣ ነፍሰጡር ሴቶች በበሽታ ላይ መውደቃቸውንም አመልከተዋል።

የኢህአደግ መንግስት በሕይወት እያለን ገድሎን በድኖቻችንን በሜዳ ላይ በትኗል የሚሉት ነዋሪዎቹ፣ በካሬ እስከ ሠላሳ ሺ ብር ድረስ የሚያጫርቱትን የአዲስ አበባ መሬት 18 ብር ብቻ ተቀብለው እንዲለቁ የታዘዙ በዙሪያችን ያሉ የኦሮሚያ አርሶ አደሮች እያለቀሱ እንደሚገኙም ገልጸዋል።ነዋሪዎቹ በደብዳቤያቸው መጨረሻ" የአለምፒክ ፌዴሬሽን በዓላማውና ባለው እሴት ሰብዓዊ መብትን ከሚጋፋ ተግባር ጋር የማይተባበር ተቋም ቢሆንም በጭካኔ ከሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት መተባባሩን ኮንነዋል።" በኢትዮጵያውያን ላይ በኦሎምፒክ ኮሚቴ ስም እያረፈ ያለውን ሊረሳ የማይችል ጠባሳ በተመለከተ በማስገንዘብ በእኛ ላይ ለሚፈጸመው ግፍ ከዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚያገኘውን ፈንድ እንዲቆምላቸው" ጠይቀዋል።ከአለማቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴው ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎችም ጉዳዩን እንዲያደርሱላቸው ተማጽነዋል። ደብዳቤውን የጻፉትን ሰዎች በስልክ አነጋግረን እንደተረዳነው፣ ደብዳቤያቸውን ከጻፉ 2 ሳምንታት ያለፈው ሲሆን፣ መንግስት የሚወሰድውን እርምጃ በመፍራት እስካሁን ይፋ ለማድረግ ሳይፈልጉ ቀርተዋል

## ቡራዩ ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ ተቃውሞ በርካታ ወጣቶችን ለእስር ዳረገ

ከአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚኖሩ ደሃ የኦሮሞ ገበሬዎችን አፈናቅሎ መሬታቸዉን ለወያኔና ለበለሟሎቻቸዉ የሚያድለዉን አዲሱን አዲስ አበባ ከተማ ፕላን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ ወጣቶችን ተከትሎ ፌዴአልና ክልል ፖሊስ ቡራዩ ከተማ ዉስጥ አግቶ ከያዛቸዉ ከ200 በላይ ወጣቶች መካከል ከ40 በላይ የሚሆኑት አሁንም ታስረው ከፍተኛ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ ሆነዉ የሚከታተሉ ምንቡ ጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ፖሊስ ይዞ ካሰራቸዉ እስረኞች ዉስጥ አብዛኞቹ በ25 ሺ ብር ወይም የከተማ መሬታቸዉን ካርታ በዋስትና እያ እንዲፈቱ ሲደረግ ገንዘብ መክፈል ያልቻሉትና ከኦነግ ጋር ግንኙነት ያላቸው ተብለው የተጠረጠሩት እንዳይፈቱ ተደርጓል። ለአንድ እስረኛ የዋስትና መብት የሚሰጠዉም ሆነ የሚከለክለዉ ፍርድ ቤትእና ሳለ ፖሊስ እራሱ ሰብሰቦ ያሰራቸዉን ሰዎች ብቻ 25 ሺ ብር እየከፈሉ ከእስር እንዲወጡ ማድረጉ ግልጽ የሆነ ዘረፋ ከመሆኑም በላይ ብዙ ሰዎችን እያነጋገረ ነዉ። በእስር ላይ ከሚገኙት 6 ሴቶች መካከል አያንቱ የምትባለዋ ወጣት እጆቿ በድብደባ መሰባበሩንና በከፍተኛ ህመም ላይ እንደምትገኝ ታውቋል።

ከዚህ በተጨማሪ ጋዲሳ እና ዳውድ ሃሰን የተባሉት እስረኞች በኦነግ አባልነት በመጠርጠራቸው በዋስ እንዳይፈቱ ተደርጓል። ጆቴ፣ ስራታ እና ስሮንሳ ፋይሳ ደግሞ የአዋሽ ባንክ ሰራተኞች ሲሆኑ እነሱም በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ስቃይ እየተፈጸመባቸው ነው። ጋዲሳ የተባለው የመንግስት ሰራተኛም ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል ይጠቀሳል። ንጉማ፣ ወጋሪ፣ ኡመድ ኡመርና ዳባ ቱፋ የተባሉትም እንዲሁ ከፍተኛ ድብደባ የተፈጸመባቸው በመሆኑ ወደ ሆስፒታል ተወስደዋል።በክልሉ ውስጥ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ተይዘው የታሰሩ ሲሆን አንዳንዶች በገንዘብ ዋስ ሲለቀቁ በርካቶች አሁንም በእስር ላይ ይገኛሉ።በሌላ ዜና ደግሞ በምስራቅና ምእራብ ወለጋ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች የሌሎችን ብሄር ሰዎች እያሰቃዩ መሆኑን ለኢሳት የሚደርሱት መረጃዎች ያመለክታሉ።

በወረዳና በዞን ደረጃ የሚሰሩ የኦህዴድ ሹሞች የሌሎች አካባቢ ተወላጆችን አቤቱታ እና ችግር ለማየት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፣ የሌሎች አካባቢ ነዋሪዎች ለከፍተኛ ችግር እየተጋለጡ መሆኑን ጠቅሰዋል።ሆን ተብሎ እንደተቀናበረ በሚያሳይ መልኩ የተደራጁ ወጣቶች ማታ ማታ በሌሎች አካባቢ ተወላጆች ቤቶች ላይ ጉዳት ሲያደርጉ ሰንብተዋል። ኢሳት ያነጋገራቸው ሰዎች እንደሚሉት የኦህዴድ ባለስልጣናት በሚዲያ ቀርበው የሚናገሩትና በተግባር እየፈጸሙ ያሉት ድርጊት የተለያየ ነው። ህወሃት ብሄሮችን እርስ በርስ በማጋጨት በአገር ውስጥ የገጠመውን አስተዳደራዊ ችግር አቅጣጫ ለማስቀየር እየሞከረ መሆኑን መዘገባችን ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚገኙ የሶማሊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎችን ከኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ጋር ለማጋጨት የተቀነባበረ ስራ እየሰሩ መሆኑን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች የላኩልን ዜና ያስረዳል። በዚህ በተለጣፊዉ ኦህዴድ አስተባባሪነት በሚካሄደዉ የተንኮል ዘመቻ የሰለጠኑ የአገዛዙ ካድሬዎች የሶማሌ ተማሪዎች ከመንግስት ጎን ቆመው የኦሮሞ ተማሪዎችን እንቅስቃቀሴ በተመለከተ መረጃ እየሰጡን ነው" የሚል አሉባልታ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ዉስጥ በማሰራጨት በሁለቱ ብሔረሰብ ተማሪዎች መካከል አለመተማመን እንዲነግስ አያደረጉ ነዉ። ይህ ጉዳይ የሶማሊ ተማሪዎችን ስጋት ላይ የጣላቸው ሲሆን፣ ተማሪዎቹ ከመንግስት ጎን አለመቆማቸውንና ወያኔ እንዲህ አይቱን ተራ አሉባልታ እየተነዛ ያለው የሁለቱን ብሄር ህዝቦች ለማጋጨት መሆኑን እየተናገሩ ነው።የተማሪዎች ወላጆች በሚነዛው ወሬ መደናገጣቸውንም ለማወቅ ተችሎአል።ጉዳዩን በማስመልከት ጥያቄ ያቀረብንለት የሶማሊ ክልል ፕሬዚዳንት አማካሪ የነበረውና የስዊድንን የአንቲገን ሽልማት አሸናፊ የሆነው አብዱላሂ ሁሴን ወሬው እንዲህ አይነቱ አሉባልታ በስፋት የሚሰራጨው የሁለቱን አካባቢዎች ተወላጆችን ለማጋጨት ነው ብሎአል። ኦህዴድ /ህወሃት የተለያዩ ብሄረሰቦችን ተወላጆች ለማጋጨት እንቅስቃሴ መጀመሩን በተመለከተ ተከታታይ ዘገባዎችን ማቅረባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## መድረክ የፊታችን ቅዳሜ ለጠራዉ የተቃውሞ ሰልፍ ህዝቡ በብዛት እንዲገኝ ጥሪ አቀረበ

ለቅዳሜ ግንቦት 16 ቀን 2006 በተጠራዉ ህዝባዊ የተቃዉሞ ሰልፍ ላይ የአዲስ አበባና የአካባቢዋ ነዋሪ በብዛት ወጥቶ የወያኔ አገዛዝ በቃን እያለ ድምጹን እንዲያሰማ መድረክ ጥሪ አቀረበ። የመድረክ የስራ አስፈጻሚ አባል አቶ ጥላሁን እንዳሻው ለኢሳት እንደተናገሩት በመጪው ቅዳሜ በሚደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ህዝቡ በብዛት ወጥቶ ችግሮቹን እንዲያሰማ ጠይቀዋል። የሰልፉ ዋና አላማ በአገራችን ለሚነሱ የመብት ጥያቄዎች የሃይል ምላሽ መስጠት ይቁም የሚል መሆኑን የገለጹት አቶ ጥላሁን፣ በኦሮምያ በተማሪዎች ላይ የተወሰደውን የሃይል እርምጃ እንደሚያወግዝም ጠቁመዋል።
መድረክ ሁለት ጊዜ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ጥያቄ አቅርቦ ቢከለከልም በመጨረሻ ግን ፈቃድ ማግኘቱን የገለጹት አቶ ጥላሁን፣ ግንቦት 16 የሚካሄደው ሰልፍ ከጧቱ 3 ሰአት ጀምሮ እስከ 6 ሰአት ድረስ ከግንፍሌ ወንዝ ድልድይ ተነስቶ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ባለው ቦታ ላይ ይካሄዳል። የአዲስ አበባ አዲሱን ማስተር ፕላን በተመለከተ መድረክ ያለህዝብ ተሳትፎ መካሄድ እንደሌለበት እንደሚያምን የገለጹት አቶ ጥላሁን፣ መንግስት በሚስጢር ይዞ የሚሰራው ስራ አሁን የታየውን ችግር መፍጠሩንና እስካሁንም ለታየው ችግር መንግስት ተጠያቂ መሆኑን ገልጸዋል።

“የተቃውሞ ሰልፎችን በጋራ ለማካሄድ ለምን አልቻላችሁም፣ መድረክ የህዝብ ግንኙነት ስራ በመስራት በኩል ድክመት እንዳለበት በገሃድ ይታያል ለዚህስ ምን ምላሽ አላችሁ ተብለው የተጠየቁት አቶ ጥላሁን፣ ከፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመስራት ጥረት ማድረጋቸውን፣ የህዝብ ግንኑነት ስራን በተመለከተም ድክመት ቢኖርባቸውም ሌሎች ሚዲያዎችም ለመድረክ በቂ ሽፋን የማይሰጡ መሆናቸውን በማንሳት ወቀሳ አቅርበዋል። በሌላ ዜና ደግሞ ከአዲ ስአበባ ማስተር ፕላን ጋር ተያይዞ የተነሳውን ተቃውሞ ለማርገብ በአዲስ አበባ የሚገኙ የጸጥታ ሃይሎች በፖለቲካና በደህነት ክትትል አቅማቸውን ለማጎልበት በሚል ስልጠና እየተሰጣቸው ነው፡፡ ከፖሊስ ጣቢያ ኃላፊ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የፖሊስ ማዕረግ ያላቸው የፖሊስ አባላት በኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛና በሰንዳፉ ፖሊስ ማሰልጠኛ ከግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ወር የሚቆይ ስልጠና እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ለመረዳት ተችሎአል።

## ፋሽስቱ ወያኔ የሶማሊ እና ኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሌላ ዜና በአዊ ዞን የተለያዩ ከተማ ነጋዴዎች በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ምሬት እየገለፁ መሆኑ ታውቋል። ሰሞኑን ባልደረባችን በዞኑ ከተሞች ተዟዙሮ ያሰባሰባቸው መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሁሉም የአዊ ዞን ከተሞች ነጋዴዎች በመልካም አስተዳደር ችግሮች እየተሰቃየ እንደሚገኙ አረጋግጧል።

አንዳንድ የዞኑ ነጋዴዎች እንደተናገሩት የአገዛዙ ካድሬዎች የሚያቀረቡዋቸው ሪፖርቶች ለራሳቸው የሚጠቅሙ እንጅ ህዝቡ የሚያያቸው አይደሉም በማለት የገለፁ ሲሆን እቃዎች ሳይገዙ እንደተገዙ ተደርጎ ይወራረዳሉ፣ ጥራት ያላቸው እቃዎች አይገዙም፣ የአገዛዙ መጋዘኖችም በሹማምንቱ ይዘረፋሉ ሲሉ አጋልጠዋል። የዞኑ የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት ከሙስና እና ከመልካም አስተዳደር ጋር በተያያዘ ክሶች ሲቀርቡባቸው እርምጃ ከሚወሰድባቸው ይልቅ ወደ ሌሎች መስሪያቤቶች ተዛውረው እንዲሰሩ እንደሚደረጉ የታወቀ ሲሆን ተቃውሞአቸውን በሚያሰሙበት ጊዜም አሻባሪዎች፣ ጸረ ህዝቦች እየተባሉ እንደሚከሰሱ በምሬት ተናግረዋል።

## ዲፕሎማቱ እራሳቸዉን አጠፉ ቢባልም የአሟሟታቸዉ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፖሊስ ኢምባሲውን በመዝጋት ካለፉት 2 ቀናት ጀምሮ ምርመራ በሰራተኞች ላይ እያደረገ ይገኛል።ዲፕሎማቱን ያገኙት የኢምባሲው ሰራተኞች ሲሆኑ ከሞተ ከአንድ ሰአት በሁዋላ አምቡላንስ በቦታው ቢደርስም የዲፕሎማቱን ህይወት ለማትረፍ እንዳልተቻለ ታውቋል።አንዳንድ ጣሊያን ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግለሰቡ ራሱን አጥፍቷል ብለው እንደማያምኑ እየተናገሩ ነው። አቶ ፍስሃ ወደ ኢጣሊያ ከመዛወራቸው በፊት በአውሮፓ ህብረት ዴስክ ኦፊሰር ሆነው ከሰሩ በሁዋላ፣ የአለማቀፍ ተቋማት ጊዜያዊ ዳይሬክተር እንዲሁም የዲያስፖራ ክፍል ዳይሬክተር ጀኔራል ሆነው ሰርተዋል። አቶ ፍስሃ የህወሃት አባል መሆናቸውን አንዳንድ ወገኖች ይገልጻሉ።